

# የ2023 የሪል ስቴት ግብር
## ግመታ መረጃ

በሕግ የፌየርፋክስ ካውንቲ በጥር 1 ቀን ሁሉም ሪልስቴቶች ላይ በ100% ፍትሀዊ የገበያ ዋጋቸው ግብር መገመት አለበት።

### የመኖሪያ ንብረቶች

ይህ በፌየርፋክስ ካውንቲ ውስጥ በ2022 የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት እንዲሁም በመላው ኖርዝ ቨርጂንያ እና ዩኤስ ውስጥ የሻጭ ገበያ ነበር። ሆኖም በበጋ እና የመኸር ወቅቶች ውስጥ የቤት ብድር ተመኖች እየጨመሩ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ ምንም እንኳን ፖዘቲቭ ቢሆንም የአመት ከዓመት የዋጋ መጨመር ተመኑ ቀንሷል። **በ2022 መጨረሻ ላይ የቤት ሽያጭ ዋጋዎች በአማካኝ አሁንም ቀደም ሲል ከነበሩት 12 ወራት የበለጡ/ከፍ ያሉ ነበሩ።** የ2023 የግብር ግምትዎን ለመወሰንም መነሻ የሆነው ይህ ነበር።

### የንግድ ንብረቶች

በ2022 ውስጥም ወረርሽኙ የቀጠለ ቢሆንም በፌየርፋክስ ካውንቲ የንግድ ሪልስቴት ሸዋጋዎች ላይ የፈጠራቸው ተጽእኖዎች አሁንም አጠራጣሪ ሆኖ ቀጥሏል። ባጠቃላይ ግን ዋጋዎች ካለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸሩ የጨመሩ ሲሆን የተወሰኑ የንብረት አይነት ዋጋዎች ደግሞ ቀንሰዋል።

## የሪልስቴት ግብሮች፡ መታወቅ ያለባቸው ዋና ዋና ቀናት

ሚያዚያ 3 – በግብር ግመታዎ ላይ አስተዳደራዊ ይግባኝ የሚያቀርቡበት የመጨረሻ ቀን

ግንቦት 1 – ለግብር እፎይታ ማመልከቻ ማብቂያ ቀነ ገደብ

ግንቦት 9 –የኃላፊዎች ቦርድ ኦፊሴላዊ የሪልስቴት ግብር ተመኖችን የሚወስንበት

ሰኔ 1 – በግብር ግምትዎ ላይ ለማመጣጠኛ ቦርድ ይግባኝ የሚያቀርቡበት የመጨረሻ ቀን

ሰኔ ማብቂያ – የሪል ስቴት ግብር ክፍያዎች የመጀመሪያ ዙር ክፍያ የሚላክበት ቀን

ሰኔ 28 – የሪልስቴት ግብር ክፍያዎች: 1ኛ ዙር ክፍያ የሚከፈልበት ቀን

ሕዳር መጀመሪያ – የሪል ስቴት ግብር ክፍያዎች ሁለተኛ ዙር ክፍያ የሚላክበት

ታህሳስ 5 – የሪልስቴት ግብር ክፍያዎች: 2ኛ ዙር ክፍያ የሚከፈልበት ቀን



## የግብር ግምትዎ ላይ ይግባኝ ማለት

በሚከተሉት ምክንያቶች በንብረትዎ የግብር ግምት ላይ ካልተስማሙ:

- ግብሩ ከፍትሀዊ የገበያ ዋጋ እላፊ በመገመቱ
- ከተመሳሳይ ንብረቶች ጋር ሲነጻጸር ወጥነት/ተመሳሳይነት ባለው መልኩ ባለመገመቱ
- የንብረት ምዝገባዎን በተመለከተ የተሳሳተ በመሆኑ

በመጀመሪያ የንብረት ዝርዝሮችዎን እና የግብር ግምቱን ለመወሰን የታዩ ተነጻጻሪ ሽያጮችን ከwww.fairfaxcounty.gov/taxes/real-estate ላይ ይመልከቱ።

ከዚያም ስለ ጥያቄዎችዎ ወይም ማወቅ የሚፈልጓቸው ጉዳዮች በተመለከተ ከካውንቲ ገምጋሚ ጋር እንዲወያዩ እንመክርዎታለን።

ይግባኝዎን እስከ ሚያዚያ 3 ድረስ ለአስተራደራዊ ይግባኝ ሊያቀርቡ፣ ወይም እስከ ሰኔ 1 ድረስ ለማመጣጠኛ ቦርድ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ይግባኝን ለማመጣጠኛ ቦርድ ከማስመዝገብ በፊት በመጀመሪያ ለአስተዳደራዊ ይግባኝ ማስመዝገብ ይመከራል።

ወደ www.fairfaxcounty.gov/taxes/real-estate በመግባት ወይም በስልክ ቁጥር 703-222-8234, TTY 711 በመደወል ተጨማሪ ይወቁ እንዲሁም የይግባኝ ቅጾችን ያግኙ።

## ቀጠሮ በማስያዝዎ ላይ እርዳታ ያግኙ

በስልክ ወይም በቪዲዮ እርዳታ ለማግኘት ቀጠሮ ያስይዙ። ቀጠሮ ለማስያዝ QR ኮዱን ስካን ያድርጉ ወይምwww.fairfaxcounty.gov/taxes/appointments ን ይጎብኙ።




የፌየርፋክስ ካውንቲ የግብር አስተዳደር መመሪያ፣ የሪልስቴት ምድብ (Fairfax County Department of Tax Administration, Real Estate Division) 12000 Government Center Parkway, Suite 357
Fairfax, VA 22035

ስልክ: 703-222-8234, TTY 711 (ለእንግሊዘኛ/ስፓኛል)
ኢሜይል: dtared@fairfaxcounty.gov
ከሰኞ - አርብ ከ8 a.m. እስከ 4:30 p.m. ሰዓት

ይህን መረጃ በአማራጭ ፎርማት ለመጠየቅ የግብር አስተዳደር መምሪያን (Dept. of Tax Administration) በስልክ ቁጥር 703-222-8234, TTY 711 ያነጋግሩ።
የፌየርፋክስ ካውንቲ (Fairfax County), Va. ዕትም። የካቲት 2023።